vic roads

እውነታ ጽሁፍ ወረቀት

# መኪና ስለመግዛትና ማስመዝገብ

## ከግዥው በፊት

- በቪክሮድ/VicRoads' የተሽከርካሪ ምዝገባ መጠየቂያ አገልግሎት በኩል ማጣራት አለብዎ። ይህ አገልግሎት ያለክፍያ በነጻ እንደሆነና መኪናዎች፣ ሞተር ብስኪሌታዎች፣ የጭነት መኪናዎች፣ ተሳቢዎችና ካራቫኖች በቪክቶሪያ ምዝገባ ላይ የመመዝገብ ይዘትን ይነግርዎታል። በተሽከርካሪ ምዝገባ መጠየቂያ አገልግሎት በኩል የተሽከርካሪን ምዝገባ ወቅታዊ፣ ጊዜ ያለፈበት፣ የታገደ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ያስችላል። እንዲሁም ስለ ተሽከርካሪው መረጃ ማለት እንደ የተሽከርካሪ መታወቂያ ቁጥር ወይም የቻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ቁጥር፣ ወይም የተሽከርካሪው አካልና ቀለም አይነት ወይም የተሰራበትን ዓመትና ዓይነት ለመለየት ያስችልዎታል። የተሽከርካሪ ምዝገባ መጠየቂያ አገልግሎትን በድረገጽ **vicroads.vic.gov.au** ላይ በመጎብኘት ማጣራት ይችላሉ።
- እንዲሁም በግላዊ ንብረት ደህንነት ምዝገባ (PPSR) ላይ ማጣራት ይችላሉ። ይህ በሃገር አቀፍ በክፍያ የሚቀርብ አገልግሎት ሲሆን አንድን ተሽከርካሪ ከመግዛትዎ በፊት ዝርዝር ሁኔታውን እንዲያጣሩ ይረዳል። ለግላዊ ንብረት ደህንነት ምዝገባ ማጣሪያ የምስክር ወረቀት ካለዎት፣ በተሽከርካሪው ላይ የገንዘብ እዳ (ስለመጨናነቁ)፣ የተሽከርካሪን ዝርዝር መረጃ (የተሰራበትና ሞዴሉ)፣ የምዝገባው ይዘት ወይም የተሰረቀ ወይም በጽሁፍ የታገደ ስለመሆኑ ማወቅ ይችላሉ። በተለፎን 1300 007 777 ደውሎ ወይም በድረገጽ **ppsr.gov.au** ላይ ስለ PPSR ማጣራት ይችላሉ።

## የተመዘገበን መኪና ስለመግዛት

### የተመዘገበን መኪና በሚገዙበት ጊዜ ማድረግ ያለብዎት:

- በመንገድ ላይ ለመጠቀም/ Roadworthiness የምስክር ወረቀት ከሺያጩ ማግኘት አለብዎ
- ከሺያጩ ጋር በመሆን የምዝገባ ማስተላለፊያ ማመልከቻ ቅጽን መሙላት። ቅጹን በድረገጽ **vicroads.vic.gov.au**, መስመር ላይ፣ በስልክ 13 11 71 ደውሎ ማግኘት ወይም ከቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል ሂዶ መውሰድ

### ምዝገባውን ወደርስዎ ስም ለማዛወር:

- ተሞልቶ የተጠናቀቀ የማዛወሪያ ቅጽን፣ በመንገድ ላይ ለመጠቀም/ Roadworthiness የምስክር ወረቀትንና ክፍያዎችን ከተሸጠ በ14 ቀናት ውስጥ ለቪክሮድ/VicRoads ማስገባት። ይህንን ለማድረግ ሁሉንም ሰነዶችንና ክፍያዎችን (ቸክ ወይም የገንዘብ ማዘዣ) በፖስታ አድራሻ፡ VicRoads, GPO Box 1644, Melbourne 3001 አድርጎ መላክ ወይም ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል ሂዶ ማስገባት ይችላሉ።
- መኪናው ከመኪና ደላላ ከተገዛ፣ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በደላላው በኩል ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ይገባሉ።

### ክፍያዎች:

- የማዛወሪያ ክፍያ
- ለሞተር ተሽከርካሪ የቀረጥ ክፍያ

ክፍያዎች ለማስላት በድረገጽ፡ **vicroads.vic.gov.au** መስመር ላይ ወይም በስልክ 13 11 71 አድርጎ ይቻላል።

### በመንገድ ላይ ለመጠቀም/ Roadworthiness የምስክር ወረቀት

- የተመዘገበ መኪናን ለመሸጥ ከተፈለገ ወይም አሮጌ መኪና እንደገና ለማስመዝገብ ከተፈለገ
- ይህ በቪክሮድ ተቀባይነት ባገኘ ለተሽከርካሪ መርማሪ ፈቃድ ባለው ብቻ መሰጠት ይችላል።
- መኪናን በመንገድ ላይ ለመጠቀም ደህንነቱን አጣርቶ ማረጋገጥ
- ይህ ማለት መኪናው ያላረጀና ከደህንነት ስጋት ጋር በተዛመደ አካላት ለመስራት መኪናው በጣም ጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ማለት አይደለም።
- ውረቀቱ ከተሰጠ በኋላ ለ30 ቀናት ዋጋ ይኖረዋል

## ያልተመዘገበ ሚኪናን ስለመግዛት

### ያልተመዘገበ መኪና በሚገዙበት ጊዜ ማድረግ ያለብዎት:

- ከሻጩ የተፈረመበትና ቀን ያለበት ደረሰኝ መውሰድ፤ ይህም የመኪና ዓይነት፣ ሞዴልና የተሽከርካሪን መታወቂያ ቁጥር (VIN) ያካተተና የሻጩንና የርስዎን ስምና አድራሻ የሚያሳይ መሆን አለበት
- ላልተመዘገበ ተሽከርካሪ ፈቃድ ለማግኘት ማቀናጀት
- በመንገድ ላይ ለመጠቀም/ Roadworthiness ምስክር ወረቀት ማግኘት
- ቀደም ሲል ለነበረ የተሽከርካሪ ምዝገባ ማስረጃ እንደ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ
- ለማስመዝገብ ቀጠሮ ማቀናጀትና መኪናውን ለማስመርመር ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል ይዞ መምጣት (መኪና ለማስመዝገብ እድሜዎ 17 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት)

#### ላልተመዘገበ ተሽከርካሪ ፈቃድ

ያልተመዘገበ መኪና ለማስጠገን ወይም በመንገድ ላይ ለመጠቀም/ Roadworthiness የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሲባል ከመንዳትዎ በፊት ላልተመዘገበ ተሽከርካሪ ፈቃድ ማውጣት አለብዎ።

- ይህ በመንገድ ለመጠቀም/ Roadworthiness የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለመንዳት እንደሚረዳና ለመኪናው የምዝገባ ዝግጅት ይረዳል።
- ለቪክሮድ/ VicRoads በስልክ 13 11 71 በመደወል ወይም በማንኛውም የቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል ሂዶ መዛት ይቻላል። የመኪናውን መግለጫ ከሞተር ቁጥሩ ጋር ወይም የተሽከርካሪውን መታወቂያ ቁጥር (VIN) ማቅረብ አለብዎ
- በቀጠሮ መሰረት ለማስመዝገብ ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ሲነዱ ካልሆነ በስተቀር፣ ላልተመዘገበ መኪና ያልተመዘገበ ተሽከርካሪ ፈቃድ ሳይኖረው መንዳት ወንጀል ነው

## መኪናን ለማስመዝገብ ማድረግ ያለብዎ:

### ቀጠሮ ማቀናጀት:

- ጊዜን ለማቀናጀትና የቀጠሮ ክፍያን ለማካሄድ ለቪክሮድ/ VicRoads በስልክ 13 11 71 መደወል (በቪዛ ወይም በማስተርካርድ ክፍያዎች ብቻ) ወይም ወደ ቪክሮድ/ VicRoads ደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል ሂዶ (በጥሬ ገንዘብ፣ በቸክ፣ ኢፍትፖስ/ EFTPOS, በቪዛ ወይም በማስተርካርድ አድርጎ ክፍያዎችን ማክሄድ)።
- ቀጠሮ በሚያቀናጁበት ጊዜ የተሽከርካሪን መታወቂያ ቁጥር (VIN)፣ የሞተር ቁጥርና የተመዘገበበት ታርጋ ቁጥር (ካለ) ማቅረብ ይኖርብዎታል

### በርስዎ ቀጠሮ በሚቀርቡበት ጊዜ:

- ለፍተሻ መኪናውን ማምጣት
- ጊዜው ያላለፈበትን በመንገድ ላይ መጠቀሚያ/ Roadworthiness የምስክር ወረቀት ማቅረብ
- የርስዎን መታወቂያ ማቅረብ (የመንጃ ፈቅድ ያስፈልጋል፣ ወይም የመንጃ ፈቃድ ከሌለዎት የተለያዩ የመታወቂያ ሰነዶችን ማሳየት አለብዎ)
- መኪናውን ህጋዊ በሆነ መልኩ ማስመዝገብ እንዲችሉ፤ የገዙበትን ደረሰኝ ለማሳየት ይዞ መምጣት
- የዋጋ መቀነሻ ካርድ ካለዎት ለቪክሮድ/VicRoads መናገር
- ክፍያውን ማካሄድ ነው

### ክፍያዎች:

- ለምዝገባ ክፍያ (በቅናሽ ዋጋ መጠን ክፍያዎች ይቀርባሉ)
- ለታርጋ ቁጥር ጉዳይ ክፍያ (ካስፈለገ)
- ለመፈተሻ ክፍያ (ካስፈለገ በአጠቃላይ ቀጠሮ በሚቀናጅበት ጊዜ ይከፈላል)
- ለትራንስፖርት አደጋ ኮሚሽን ክፍያ (TAC) (ለሶስተኛ አካል የግለሰብ ጉዳት ዋስትና ግዴታ ይከፈላል)
- ለሞተር ተሽከርካሪ ቀረጥ ክፍያ

በድረገጽ **vicroads.vic.gov.au** መስመር ላይ ወይም ስልክ 13 11 71 በመደወል ክፍያዎችን ለማስላት ይቻላል።

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ vicroads.vic.gov.au ላይ መጎብኘት ወይም በስልክ 13 11 71 መደወል ወይም ወደ ቪክሮድ/VicRoads የደንበኛ አገልግሎት ማእከል በአካል መሄድ ነው።**

*በዚህ እውነታ ጽሁፍ ወረቀት ውስጥ የቀረበው መረጃ በሚታተምበት ጊዜ ትክክል እንደሆነና ከዚያም ሊቀየር ይችላል።*

VRPIN02900 Buying and Registering a Car – Amharic Authorised by VicRoads, 60 Denmark Street, Kew, 3101